**የ Massachusetts ኮመንዌልዝ**
**የጤናና ሰብዓዊ አገልግሎቶች ሥራ አስፈጻሚ ቢሮ**
**የእድገት አገልግሎቶች መምሪያ**
**የኦቲዝም ዲቪዥን**
**40 Broad Street - 4th Floor - Boston - MA 02109**

ነሃሴ 2026

ውድ የማህበረሰብ አቅራቢ

እርስዎም እንደሚያውቁት የእድገት አገልግሎቶች መምሪያ (DDS) የኦቲዝም ዲቪዥን **ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት መተዊያ ፕሮግራም (Children's Autism Waiver Program)** ተብሎ የሚጠራ ፕሮግራም ያካሂዳል። ይህ ፕሮግራም **ዕድሜያቸው ከ10 ዓመት በታች ለሆኑ** MassHealth መደበኛ ኢንሹራንስ ያላቸው ወይም የሚያገኙ ህጻናትን ጨምሮ የህክምናና የፋይናንስ ብቁነትን ለሚያሟሉ ህጻናት ግልጋሎት ይሰጣል። በአሁኑ ወቅት ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት መተዊያ ፕሮግራም በዓመት ወደ 500 ለሚጠጉ ህጻናት ግልጋሎት ሊሰጥ ይችላል። ፕሮግራሙ ዕድሜያቸው 3 ዓመት ለሞላቸው እና ከቅድመ ጣልቃገብነት ለሚሸጋገሩ ህጻናት የመጠባበቂያ አቅም (በመላው ግዛቱ ውስጥ 55 ስሎቶች) አሉት። ሁሉም የመተዊያ አገልግሎቶች ህጻኑን ለመተዊያ ፕሮግራሙ በምዝገባ ወቅት ውስጥ በሙሉ የፋይናንስ እና የህክምና ብቁነት መስፈርቶቹን በማሟላቱ መቀጠል እንዳለበት ይጠይቃሉ። በፕሮግራሙ ውስጥ በየዓመቱ ከፍተኛ መጠን ያለው መቀያየር ያለ በመሆኑ ምክንያት ከዚህ የመክፈቻ ጥያቄ ዝርዝር ወደ ክፍት ስሎቶችን መሙላት እናልፋለን።

ዛሬ ስለመጪው ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት መተዊያ ፕሮግራም **ክፍት የመጠየቂያ ጊዜ** በተመለከተ ይህን በማሰራጨት ረገድ የእርስዎን እርዳታ እንጠይቃለን። የኦቲዝም ዲቪዥኑ ለዚህ ፕሮግራም ካላቸው ቤተሰቦች **ከጥቅምት 16፣ 2026 እስከ ጥቅምት 30፣ 2026** ባሉት ቀናት ውስጥ **አዲስ የማመልከቻ ጥያቄዎችን ይቀበላል**። ማመልከቻዎቹ የፖስታ ምልክት የተደረገባቸው መሆን አለባቸው ወይም እስከ ኦክቶበር 30, 2026 ከወላጅ/ አሳዳጊ በኢሜይል መላክ አለባቸው።

ይህ ቤተሰብ እና ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶችን መተዊያ ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናትን በቤተሰባቸው ውስጥ እንዲቆዩ እና በቤተሰባቸውና ማህበረሰባቸው ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ለመርዳት የተዘጋጀ የMedicaid ፕሮግራም ነው። ይህ ፕሮግራም ከፌደራሉ መንግስት በከፊል የገንዘብ ድጋፍ ይደረግለታል። የመተዊያ አገልግሎቶች በIDEA (የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ) ስር የሚቀርቡት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ተጨማሪ ሲሆኑ በፕሮግራሙ እየተደገፈ እያንዳንዱ ቤተሰብ ለልጁ የተገመገሙ ፍላጎቶች ድጋፍ ለማድረግ በቤተሰቡ በሚመረጠው የህክምና ሞዴል ላይ ተመስርቶ በግል የሚዘጋጅ የአዎንታዊ ባህሪ ድጋፍ ዕቅድ የሚያዘጋጅ ልዩ ሙያ ያለው የህክምና ባለሙያ መቅጠር፣ እና በዕቅዱ ውስጥ የተመደበ የአንድ ለአንድ ጥብቅ ህክምና የሚያቀርብ ቀጥተኛ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ መቅጠር ይጠበቅበታል። በፕሮግራሙ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች በተጨማሪም እንደ የማህበረሰብ ውህደት ተግባሮች፣ የቤተሰብ ስልጠናና የፋታ አገልግሎት ያሉ ልጆቻቸውን ከባህሪ፣ ማህበራዊ ክህሎቶችና ግንኙነት ጋር ተያያዥነት ባላቸው መስኮች ላይ እድገት እንዲያመጡ ለመርዳት የተዘጋጁ ሌሎች የመተዊያ አገልግሎቶችን የሚመርጡበት ዕድል አላቸው።

**ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት መተዊያ ፕሮግራም ክፍት የመጠየቂያ ማመልከቻ እና ክፍት የመጠየቂያ የቤተሰብ መልዕክት** ኮፒ በእንግሊዘኛ ተያይዟል። የማመልከቻ ቅጹ፣ የቤተሰብ ማስታወቂያ፣ እና ተያያዥ ሰነዶች (በተለያዩ ቋንቋዎች*) በተጨማሪም በDDS ድረገጽ ላይ በ፡ DDS ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት መተዊያ አገልግሎት ፕሮግራም አጠቃላይ መግለጫ | Mass.gov እና በሰባት ክልልን መሰረት ያደረጉ የኦቲዝም ድጋፍ ማዕከላት ይገኛሉ (የማዕከላት ዝርዝር በDDS ድረገጽ ላይ ይገኛል)። በተጨማሪም ማመልከቻውን በኦንላይ ለመሙላት በሚከተለው ማስፈንጠሪያ ላይ ቀርቧል፡ 2026 ክፍት የፍላጎት መጠየቂያ ማመልከቻ። እባክዎ ስለዚህ ማመልከቻ ሂደት በተመለከተ ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎ ሳያመነቱ የኦቲዝም ዲቪዥኑን በ፡ DDS-ChildrensAutismWaiverProgram@mass.gov ወይም የአካባቢዎን የኦቲዝም ድጋፍ ማዕከል ያነጋግሩ። እባክዎ ይህ አዲስ የኢሜይል አድራሻ እንደሆነ ልብ ይበሉ።

ከሰላምታ ጋር፣

Mary Kate Haswell
**ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት መተዊያ ፕሮግራም ሥራ አስኪያጅ**

Stephanie Coburn
**ኦቲዝም ያለባቸው ህጻናት መተዊያ ፕሮግራም ሥራ አስኪያጅ**